# 3. ሕይወት ምንድን ነው?

- **በዚህ ክፍለ ትምህርት የሚከተሉትን ነገሮች ይማራሉ**
  - ለምን ዓላማ ተወለዱ?
  - እግዚአብሔርን የሚያከብሩት እንዴት ነው?
  - እግዚአብሔርን የሚመስሉት እንዴት ነው?
  - ምን ዓይነት ሰው መሆን ይፈልጋሉ?
  - የእግዚአብሔር ልጅ መሆንዎን እንዴት ያወቃሉ?

## ክፍል 1

### ለምን ዓላማ ተወለዱ?

**ለምን እንደተወለዱ ማወቅ አለብዎ**

አንድ ሰው የፕላስቲክ ሳህንን እንደ ምግብ መቀቀያ፣ ብርጭቆን ደግሞ እንደመዶሻ ለጠቀምበት ሲሞክር ቢያዩ ምን ሊያስቡ ይችላሉ? ዓላማውን ሳያውቅ ሕይወቱን በሙሉ ያባከነ ሰው ሲያዩ ምን ለሰሙዎ ይችላል? ሕይወታችንን ለተፈጠረበት ዓላማ ማዋል እስካልጀመርን ድረስ በዕሳት ላይ የተጣደ የፕላስቲክ ሳህን ወይም እንደ ብርጭቆ መዶሻዎች መሆናችን ነው፡፡ ህይወታችን ያለምንም እርካታ እና መሳካት ያልፋል፡፡

እግዚአብሔር ለህይወትዎ ዓላማ እና እቅድ አለው፡፡ በምድር ላይ እንዳሰሩት የሚፈልገው ስራ አለ፣ በሰማይም ድንቅ መኖሪያ ቤትን አዘጋጅቶልዎታል፡፡ በእግዚአብሔር እቅድ ወስጥ ገብተው ለመኖር ተወልደዋል፡፡

**የእግዚአብሔር ልጅ ለመሆን ተወልደዋል**

እግዚአብሔርን ደስ ለማሰኘት፣ ልጁ ለመሆን፣ በፍቅሩ ደስ ለሰኙ፣ እና እርሱን ደስ ለማሰኘት እንደተፈጠሩ ተምረዋል፡፡ ስለዚህ ምንም ነገር ቢያደርጉ ከእግዚአብሔር ጋር ህብረት ከሌለዎት የህይወትዎን ዋና ዓላማ አጥተዋል፡፡

መዝ 16፥11 «የሕይወትን መንገድ ታሳየኛለህ፣ በአንተ ዘንድ የደስታ ሙላት፣ በቀኝህም የዘላለም ፍስኃ አለ»፡፡

**እግዚአብሔርን በመምሰል እንዲያድጉ ተወልደዋል፡፡**

የእግዚአብሔር ልጅ ለሆኑት ለእርስዎ በምድር ላይ ያለው ህየወትዎ ለዘላለም ህይወት የሚዘጋጁበት ትምህርት ቤት ነው፡፡ ልምምዶችዎ በእግዚአብሔር መንግስት ወስጥ ለሚኖርዎ ድርሻ የሚያስተምሩ ነገሮች ናቸው፡፡ አሁን የሚያጋጥምዎት ችግሮች እና ወጣወረዶች ትዕግስትን፣ እምነትን እና መታዘዝን ሊያስተምሩዎ ነገሮች ናቸው፡፡ በመንፈሳዊ ህይወትዎ በሳል እንዲሆኑ እና የበለጠ የሰማዩን አባትዎን

እንዲመስሉ ይረዳዎታል፡፡ እግዚአብሔር አሁንም ሆነ ወደፊት የሚጠቀምብዎ ታማኝ ሰው ያደርግዎ ዘንድ ይፍቀዱለት፡፡

2ጢሞ 2፡12 «ብንፀና ከእርሱ ጋር ደግሞ እንነግሳለን»

**ከእግዚአብሔር ጋር ለመስራት ተወልደዋል፡፡**

በነበሩበት ጊዜ፣ በነበሩበት ቦታ እና በነበረዎ ማንነት የተወለዱት ለቤተሰብዎ ለአካባቢዎ፣ ለአገርዎ፣ እና ለዓለም ሁሉ በረከት እንዲሆኑ ነው፡፡ እግዚአብሔር የእርሱ አጋር በመሆን አብረው እንዲሰሩ ይፈልጋል፡፡ ሌሎችን ወደ አየሱስ ክርስቶስ እንዲመሩ እና በእርሱ በኩል ወደሚገኝ የተሻለ ህይወት ወስጥ እንዲመጡቸው ያግዛል፡፡

> **ኤፌ** 2፡10 «ምክንያቱም እግዚአብሔር አስቀደሞ ያዘጋጀልንን መልካም ስራ እንድንሰራ በክርስቶስ አየሱስ የተፈጠርን የእግዚአብሔር እጅ ስራዎች ነን፡፡»
>
> **የሚከተሉትን ይስሩ**

- እግዚአብሔር ህይወት የሰጠኝ የእርሱ . . . . እንደሆን፣ በእርሱ . . . . እንዳድግ፣ እና ከእርሱ ጋር ተባባሪ በመሆን አብሬው ______________ ለመሆን ነው፡፡
- *ራስዎን ይጠይቁ*
- በእርግጥ ህይወቴ እግዚአብሔርን ያስደስታል?
- መከራና ወጣ ወረዶች በህይወቴ ትዕግስትን እና መልካም ስነ ምግባርን የሚያመጡ አጋጣሚዎች ናቸው ብዬ እቀበላለሁ?
- ሌሎችን ለመርዳት ሚድረግ የምችለውን እያደረኩ ነወ?
- የምኖረው ኑሮ ሞት የሁሉ ነገር መጨረሻ እንደሆነ በማሰብ ነው ወይስ ለዘላለም ህይወት ዝግጅት ህይወቴን እየተጠቀምኩበት ነው?
- ከእግዚአብሔር ጋር ህብረት በሚድረግ ደስ ይለኛል?
- በቤቴ እና በአካባቢዬ የእግዚአብሔርን እቅድ መከተል ጀምሬአለሁ?

# ክፍል 2

## እግዚአብሔርን የሚመስሉት እንዴት ነው?

**እግዚአብሔር በአምሳሉ የተፈጠረ መንፈስ ሰጥቶዎታል፡፡**

እግዚአብሔር አዳምን ከምድር አፈር ሰርቶ እንደሌሎች ምድራዊ ፍጡሩን አይነት ተፈጥሮ ሰጠው፡፡ ይህን ምድራዊ ተፈጥሮ እርስዎም ወርሰዋል፡፡ የአዳም ወስጣዊ ህይወት፣ መንፈሱ የመጣው ከእግዚአብሔር እስትንፋስ ነው፡፡ የአዳም መንፈስ እግዚአብሔርን የሚመስል ነበር፡፡ የእርስዎም መንፈስ በብዙ መልኩ እግዚአብሔርን ይመስላል፡፡

**ይህን ጥቅስ በቃልዎ ይያዙ፡፡**

ዘፍጥረት 1፡ 26፤ 2፡ 7 እግዚአብሔር «ሰውን በመልካችን ፣ በአምሳላችን እንስራ» በማለት «እግዚአብሔር አምላክ ከምድር አፈር ወስዶ ሰውን አበጀው በአፍንጫው የህይወትን እስትንፋስ እፍ አለበት ሰውም ሕያው ነፍስ ሆነ»

በወስጥዎ ያለው የእግዚአብሔር ምሳሌ በብዙ መንገዶች ታይቷል፡፡ ይህ ልዩ መንፈስ ከእንስሳት የተለዩ ያደርግዋል፡፡ ይህን በሰው ወስጥ ያለ የእግዚአብሔር መልክ የእግዚአብሔር አምሳል ብለን እንጠራዋለን፡፡

- በእርስዎ ወስጥ ያለውን የእግዚአብሔርን አምሳል በሚከተሉት ነገሮች ወስጥ ሟየት ይችላሉ
- ግበረገባዊ ተፈጥሮዎ መልካሙን እና ክፉን ለመለየት ይረዳዎታል፣
- የአደናቂነት ተፈጥሮዎና ወበትን መወደድዎ፣
- የማስብ ችሎታ ያለው ተፈጥሮዎ እውነትን ለማወቅ ያለዎ ፍላጎት፣ የማገናዘብ ችሎታዎ፣ የንግግር ችሎታዎ እና ማባባት መቻልዎ፣
- መንፈሳዊ ተፈጥሮዎ እግዚአብሔርን ለማምለክ ያለዎ ፍላጎት እና ከእርሱ ጋር ህብረት የሚደረግ ችሎታዎ፣

የፈጠራ ችሎታዎ አካባቢዎን ለማሻሻል ያለዎ ፍላጎት ሰው ወንዞችን ጠልፎ የመጠቀም፣ የኤሌክትሪክ ኃይል ማመንጨት እና የሚጠቀምባቸውን መሳሪያዎች የመፈልሰፍ ችሎታ አለው፡፡ በሙዚቃ ወስጥ ወበትን መፍጠር፣ ስነጥበባዊ ስራዎች፣ ግጥሞች፣ ዝማሬዎች፣ ወዛዋዜዎችን ሁሉ መፍጠር ይችላል፡፡

| |
|---|
| እነዚህ ነገሮች የሚመጡት ከእግዚአብሔር ተፈጥሮ ሲሆን ከእንስሳት ልዩ ያደርጉናል፡፡<br>የእግዚአብሔር ልጅ እንዲሆኑና በህይወትዎም ልዩ ዓላማ እንዳለው ያሳዩዎታል፡፡<br>**የሚከተሉትን ይስሩ**<br>እግዚአብሔር በሰዎች ወስጥ ያስቀመጠው መንፈስ የእርሱ ＿．．．＿ ነጸብራቅና ከ ＿．．．．．＿ የተለየን ያደርገናል፡፡ |

በሰው ወስጥ የእግዚአብሔር አምሳል ወበትን በመወደዱና በ ＿．．．．．．＿ ተፈጥሮው፣ በማገናዘብ ችሎታው ወይም በ． ＿．．．＿ ተፈጥሮው፣ በመፈልሰፍ ወይም በመፍጠሩ መልካምን እና ክፉን በሚያውቁው ተፈጥሮው፣ እግዚአብሔርን በመፈለጉ ወይም ＿．．．．＿ ተፈጥሮው እንመለከታለን፡፡

እነዚህ ችሎታዎች ከሌሎች የእግዚአብሔር ፍጥረቶች የተለዩ እንደሚያደርጉዎ መረዳት ይችላሉ፡፡ እግዚአብሔር በሰጠዎ ችሎታ ያደረጉትን አንድ ነገር እንደምሳሌ ያስቡ፡፡ ሌላ ፍጥረት የሌለውን ብዙ ሐሳብና ኃይል ይዘዋል፡፡ ዝንጀሮ መጽሐፍ መጻፍ አይችልም፣ አንበሳ አወሮፕላን ማብረር አይችልም፡፡ እግዚአብሔርን እንዲመስሉ ስለሚያደርግ ስለ እያንዳንዱ ተፈጥሮዎ እግዚአብሔርን ያአመስግኑ፡፡

# ክፍል 3

## እግዚአብሔርን የሚመስሉት እንዴት ነው?

**ቁስ አካላዊ አካል አለዎ**

እግዚአብሔር ወሰን የሌለው፣ ዘላለማዊና ሁሉን ቻይ የሆነ መንፈስ ነው፡፡ በቦታም ሆነ በጊዜ አይወሰንም፡፡ አይሞትም፡፡ የእርስዎ መንፈስ ግን የሚኖረው ወሰን አቅም ባለው፣ በአንድ ቦታ ላይ ብቻ ማኘት በሚችል እና አንድ ቀን በሚሞት አካል ወስጥ ነው፡፡ ይህን እንጂ ከእግዚአብሔር የተሰጠዎ ደንቅ ስጦታ ነው፡፡ አካል ስላለዎ መንፈስ ብቻ ቢሆኑ ኖሮ ሊሰሩት የማይችሉትን ነገር ለእግዚአብሔር ማቅረት ይችላሉ፡" አካልዎ የመንፈስዎ መኖሪያ እና እግዚአብሔር የሚጠቀምበት መቅደስ ስለሆነ ጥንቃቄ ሚዊግ አለብዎ፡፡

**1ቆሮ** 6፡ 19፡ 20 «ለመሆኑ ሰውነታችሁ በወስጣችሁ የሚኖረው የመንፈስ ቅዱስ ቤተ መቅደስ እንደሆነ አታውቁምን ስለዚህ በሰውነታችሁ እግዚአብሔርን አክብሩ፡፡»

አንዳንድ ሰዎች ለማያደርጓቸው መጥፎ ነገሮች በሰውነታቸው ያሳብባሉ፡፡ በራሳቸው መልካም ለማድረግ ብለዉ ሰውነታቸውን ይቀጣሉ፡፡ አካልዎ በራሱ ጥሩ ወይም መጥፎም አይደለም፡፡ እርስዎ የሚጠቀሙበት መሳሪያ ነው፡፡ ምን ሚድረግ እንደሚፈልጉ ይወስናሉ ሰውነትዎ ደግሞ ይፈጽማል፡፡ ሰውነትን ለመልካም ወይመ ለክፉ፣ ለሰይጣን ወይም ለእግዚአብሔር ሊጠቀሙበት ይችላሉ፡፡

**ሮሜ** 12፡ 1 «እንግዲህ ወንድሞች ሆይ ሰውነታችሁን ቅዱስና እግዚአብሔርን ደስ የሚያሰኝ ሕያው መስዋእት አድርጋችሁ ታቀርቡ ዘንድ በእግዚአብሔር ርህራሔ እለምናችኋለሁ፡፡»

ሰውነትዎን መቆጣጠርዎን እርግጠኛ ይሁኑ፡፡ ጥሩ አገልጋይ ነወ፤ ነገር ግን በጣም ደካማ ጌታ ነው፡፡ አካላዊ ፍላጎቱ ህይወትዎን እንዲገዛ ከፈቀዱለት ችግር ወስጥ ይገባሉ፡፡ እንዲያወም ለአንዳንድ መጥፎ ልምዶች ተገዢ በመሆን ራስዎን ሊጎዱና ርኩሰት የሆኑ ነገሮችን በመፈጸም እግዚአብሔርን ሊያሳዝኑ ይችላሉ፡፡ የመንፈሳዊ ተፈጥሮዎን ፍላጎት ቸል በማለት የሰውነትዎን ፍላጎት ለማርካት ብቻ ከኖሩ እግዚአብሔርን የመምሰልዎ ነገር እየደበዘዘ ይሄዳል፡፡

## ሐጢአት ተፈጥሮዎን አበላሽቶታል

ሐጢአት በወስጥዎ ያለውን የእግዚአብሔር ምሳሌ አበላሽቶታል፡፡ ሰዎች የራሳቸውን ህይወት ለመምራት ሲሞክሩ እና እግዚአብሔር ያዘጋጀላቸውን ዓላማ ሲተው እየባሰባቸው ይሄዳል፡፡

**ገላቲያ** 5፡ 19 21 «የሥጋ ስራ ግልጽ ነው፡፡ ይህወም ዝሙት፣ ርኩሰት፣ መዳራት፣ ጣ ዖትን ማምለክ፣ ሟርት፣ ጥላቻ፣ ጠብ፣ ቅናት፣ ቁጣ፣ ራስ ወዳድነት፣ መለያየት፣ አድመኝነት፣ ምቀኝነት፣ ስካር፣ ዘፋኝነት፣ እንዲህም፣ እነዚህን የመሰለው ነው፡፡ አስቀድሜ እንዳልሁ አሁንም አስጠነቅቃችኋለሁ በእንደዚህ ሁኔታ የሚኖሩ ሁሉ የእግዚአብሔርን መንግስት አይወርሱም፡፡»

## በራስዎ ጥረት እግዚአብሔርን ደስ ማሰኘት አይችሉም

እግዚአብሔር ለእርስዎ መልካም ዓላማ ዓለው፡፡ ነገር ግን እርሱ ካላገዘዎ በስተቀር ሊከተሉት አይችሉም፡፡ ምንም ያህል በርትተዉ ቢሞክሩ እርሱን ደስ የሚያሰኘውን ነገር ሁልጊዜ ለማድረግ የሚያስችል ጉልበት አይኖርዎትም፡፡ እርሱ ለለውጥዎ ያስፈልጋል፡፡

**ሮሜ** 7፥ 18-20 «በእኔ ማለትም ኃጢአተኛ በሆነው ተፈጥሮዬ ወስጥ ምንም በጎ ነገር እንደማይኖር አወቃለሁ በጎ የሆነውን የማድረግ ምኞት አለኝ ነገር ግን ልፈጽመው አልችልም፡፡ የማደርገው ላደርገው የምፈልገውን በጎ ነገር አይደለም ዳሩ ግን ለማድረግ የማልፈልገውን ክፉ ነገር ነው፡፡»

## እግዚአብሔርን ከመምሰል በእጅጉ የራቁ ስለሆኑ በወስጥዎ ሊታደሱ እና ሊለወጡ ይገባል፡፡

ወደ ቤተክርስቲያን በመሄድ ወይም ጥሩ ሰው በመሆን በማያደርጉት ጥረት ብቻ ራስዎን መለወጥ አይችሉም፡፡ የእግዚአብሔር እርዳታ ያስፈልግዎታል፡፡ ከፈቀዱለት የእርሱን ባህሪ በወስጥዎ እንደገና ይሰራ ዘንድ መንፈስ ቅዱስን ይልካል፡፡ ያን ጊዜ ብቻ ነው እርሱን ደስ ማሰኘት የሚችሉት፡፡

**የሚከተሉትን ይስሩ**

- እንደ እግዚአብሔር የሚይመስሉባቸውን ነገሮች ሲማሩ ይህን ክፍል እንደገና ያንብቡ፡፡ በህይወትዎ ወስጥ እንዲኖር በሚይፈልጉት ነገር ላይ ያስምሩበት፡፡
- ሰወነታችን ከእዚአብሔር የሆነ ደንቅ . . . . . ______________________ነው፡፡
- . . . . . . . ______ ህይወታችንን እንዲገዛ ከፈቀድንለት እግዚአብሔርን መምሰላችን እየቀነሰ ይሄዳል፡፡

በራስዎ ጥረት እግዚአብሔርን ደስ ማሰኘት ይችላሉን?

# ክፍል 4

## ምን ዓይነት ሰው መሆን ይፈልጋሉ?

አንድ ሸክላ ጥራት ያለው ወይም የሌለዉ ዕቃ ሊሆን ይችላል፡፡ ወጤቱ የሚወሰነው በባለቤቱ ፍላጎት እና በሸክላ ሰሪው መያ ነው፡፡ የሰው ተፈጥሮ ብቻውን ከተተወ ከመጥፎነት አልፎ ወደከፉ ነገር እየባሰበት ይሄዳል፡፡ በቆሻሻ ነገር የተሞላ የጥላቻ ሐሳብ እና ክፉ ተግባር የሞላበት ይሆናል፡፡ ይሁን እንጂ ጥበበኛ በሆነው ሸክላ ሰሪ በእግዚአብሔር እጅ ከሆነ ግን ህየወትዎ የአስደናቂ ወበት ጠቃሚነት ምሳሌ ይሆናል፡፡

**ሮሜ** 12፥ 2 «መልካም ደስ የሚያሰኝ ፍጹም የሆነውን የእግዚአብሔርን ፈቃድ ምን እንደሆነ ፈትናችሁ ታወቁ ዘንድ በአእምሮአችሁ መታደስ ተለወጡ እንጂ ይህን አለም አትምሰሉ፡፡

**የሚከተሉትን ይስሩ፡፡**

እግዚአብሔር ወስጥዎን እንዲያደስልዎ እና እንዲለወጥዎ ይፈልጋሉ?

በራስዎ አባባል እንዲያደርግልዎ ይጠይቁት፡፡

ክርስቲያን ከሆኑ ደግሞ እግዚአብሔርን መምሰል ይፈልጉ ይሆናል፡፡ ይህ ከሆነ ለእርሱ ይንገሩ እና እንዲረዳዎ ይፀልዩ፡፡

# ክፍል 5

## የእግዚአብሔር ልጅ መሆንዎን እንዴት ያወቃሉ?

- አያሱስ ክርስቶስን አዳኝዎ አድርገዉ በሚቀበሉበት ደቂቃ ወስጥ እግዚአብሔር ልጁ አድርጎ ይቀበልዎታል፡፡ ይህን ደግሞ በሚከተሉት ሶስት መንገዶች ያሳወቃል፡፡
- ስለዚህ በሚናገረው በቃሉ አማካኝነት
- መንፈስ ቅዱስ በወስጥዎ በሚሰጥዎ ሚረጋገጫ እና ምስክርነት
- በህይወትዎ በሚሆናው ለወጥ፡፡

**ሮሜ** 12፣ 1 «እንግዲህ ወንድሞች ሆይ ሰዉነታችሁን ቅዱስና እግዚአብሔርን ደስ የሚያሰኝ ሕያዉ መስዋዕት አድርጋችሁ ታቀርቡ ዘንድ በእግዚአብሔር ርህራሔ እለምናችኋለሁ»

**1ዮሐ** 5፣ 10-12 «በእግዚአብሔር የሚያምን ሁሉ በልቡ ምስክር አለው. . .ምስክርነቱም ይህ ነወ፤ እግዚአብሔር የዘላለም ሕይወት ሰጠን፤ ይህም ሕይወት ያለዉ በልጁ ነው፡፡»

**ሮሜ** 8፣ 16 «የእግዚአብሔር ልጆች መሆናችንን ያ መንፈስ ራሱ ከመንፈሳችን ጋር ሆኖ ይመሰክርልናል፡፡ »

<u>**ክፍለ ትምህርት 3 ን ስላጠናቀቁ እን•ን ደስ አለዎ!**</u>

**የክፍል ትምህርት 3ን ጥያቄዎች በዚህ መጽሐፍ መጨረሻ ገጽ ላይ ከሚገኘው የክፍለ ትምህርት መልለሻ ጥያቄዎች ወስጥ መልሳቸወን ይስጡ፣ ከዚþያም ወደ ክፍለ ትምህርት 4 በመግባት ጥናትዎን ይቀጥሉ፡፡**

*እግዚአብሔር አብዝቶ ይባርክዎ!*